# Alexandria City Public Schools

## የቤተሰብ ሕይወት ትምህርት 9ኛ ክፍል

***የመገምገም መብት፡*** ወላጆች እና አሳዳጊዎች በትምህርት ክፍሉ የሚሰጠውን የቤተሰብ ሕይወት ትምህርት ፕሮግራም (Family Life Education Curriculum) የመገምገም መብት አላቸው፣ ይህም በፕሮግራሙ ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውሉ የጽሑፍ እና የድምጽ-ምስል ትምህርታዊ ቁሳቁሶችን ይጨምራል። በተጨማሪም ወላጆች እና አሳዳጊዎች ልጃቸውን ከቤተሰብ ሕይወት ትምህርት ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የማስቀረት መብት አላቸው።

***የፕሮግራም ግቦች፡*** የAPCS (የአሌክሳንድሪያ ሲቲ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች) የቤተሰብ ሕይወት ትምህርት ሥርዓተ ትምህርት የተዘጋጀው ሁሉን አቀፍ የሆነ፣ ከK-12 (ከኬ-12ኛ ክፍል) ቅደም ተከተሉን የጠበቀ እንዲሁም ለዕድሜ ተስማሚ የሆነ መመሪያን ያካተተ የቤተሰብ አኗኗር እና የማህበረሰባዊ ግንኙነቶች ትምህርትን ለማቅረብ ነው። ትምህርቱ የወላጅ ተሳትፎን ለማሳደግ፣ አዎንታዊ የራስን ፅንሰ-ሀሳቦችን ለማጎልበት እና እንደ ተማሪዎቹ የእድገት ደረጃ እና ችሎታ የእድሜ እኩዮችን ግፊትም ሆነ የዘመናዊ ኑሮ የሚያስከትላቸውን ጭንቀቶችን ለመቋቋም የሚያስችሉ ስልቶችን ለማቅረብ ታስቦ የተዘጋጀ ነው።

*የፕሮግራም ቅደም ተከተል፡* በቨርጂኒያ የትምህርት መምሪያ መመሪያ መሠረት፣ የACPS የኬ-10ኛ ክፍል የቤተሰብ ሕይወት ትምህርት ሥርዓተ ትምህርት Standards of Learning (**የትምህርት ደረጃ መስፈርት**) ላይ የተመሰረተ እና የሚከተሉትን ዘርፎችን ያካተተ ነው።

1. የቤተሰብ ኑሮ እና የማህበረሰባዊ ግንኙነቶች፤
2. የቤተሰብ ግንኙነት እሴቶች፤
3. ከጾታዊ ድርጊቶች የመታቀብ ጥቅም
4. ከጾታዊ ግኝኙነት የመታቀብ ትምህርት
5. የጋብቻ ጥቅሞች፣ ተግዳሮቶች፣ ኃላፊነቶች እና እሴቶች ለወንዶች፣ ለሴቶች፣ ለህፃናት እና ለማህበረሰቦች
6. የሰው ልጅ ጾታዊ ግንኙነት፤
7. የሰው ልጅ መራባት፤
8. ያልታሰበ እርግዝና ሲከሰት ጉዲፈቻን እንደ አዎንታዊ ምርጫ የመምረጥ ጥቅሞች፤
9. በግብረ ሥጋ ግንኙነት የሚተላለፉ በሽታዎች መንስኤ፣ መከላከል እና ተፅዕኖ፤
10. ሕገ ወጥ የሰዎች ዝውውርን መከላከል፤
11. የፍቅር ቀጠሮ ወቅት ጥቃት፣ ይህም ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ከጾታዊ ድርጊት በፊት ፈቃደኝነትን መግለፅ እንደሚያስፈልግ ማሳወቅ ላይ ማተኮርን ይጨምራል፣ ጥቃት የሚያደርሱ ጓደኝነት ባህሪያት፣ የጾታዊ ጥቃትን ለመከላከል የሚወሰዱ እርምጃዎች፣ የምክር እና የህግ አገልግሎቶችን የማግኛ መንገዶች መኖራቸውን ማወቅ፣ እና የጾታዊ ጥቃት በሚከሰትበት ጊዜ ወዲያውኑ የሕክምና እርዳታ እና ምክር የማግኘት እንዲሁም የሕጉ መስፈርቶች አስፈላጊነት፤ እና
12. የአእምሮ ጤና ትምህርት እና ግንዛቤ።

***የሥርዓተ ትምህርት ዘርፎች፡-*** *ሥርዓተ ትምህርቱ የተገነባው በሦስት የመለኪያ ርዕሶች ዙሪያ ሲሆን እነዚህም በፕሮግራሙ ልብ ውስጥ ዘላቂ ግንዛቤዎችን እና መሠረታዊ ሂደቶችን ላይ ያተኮሩ ጭብጥ ያላቸው ዘርፎች እና የሂደት ደረጃዎች ናቸው።*

1. ዋና ፅንሰ ሀሳቦች
2. ራስን ማስተዳደር
3. ግንኙነቶች
4. የግል ደህንነት

የእያንዳንዱ ክፍል የዝውውር ግቦች እና የአፈጻጸም ግምገማዎች ከእነዚህ የልኬት ርዕሶች ጋር የተጣጣሙ ናቸው።

*በአጠቃላይ የትምህርት መርሃ ግብር እይታ፡-* የሚከተሉት ርዕሶች በ9ኛ ክፍል የFLE ትምህርት ወቅት ይዳሰሳሉ።

# ፱ኛ ክፍል የቤተሰብ ሕይወት ትምህርት

| | | |
|---|---|---|
| | <u>ክፍል 1:</u> ዋና ጽንሰ ሃሳቦች<br><br>በዚህ ክፍል ተማሪዎች የወንድ እና የሴት የመራቢያ ስርዓቶችን ይማራሉ፣ የታዳጊዎች ጤና ማዕከልን ሚና ያውቃሉ፣ ስለ ወሊድ መቆጣጠሪያ ዓይነቶችን፣ በግብረ ሥጋ ግንኙነት የሚተላለፉ በሽታዎች፣ በግብረ ሥጋ ግንኙነት የሚተላለፉ በሽታዎች፣ በግብረ ሥጋ ግንኙነት በሚተላለፉ በሽታዎች መታመም፤ እና እርግዝና መከላከያ ዘዴዎች ይማራሉ።<br><br>1. ትምህርት 1፡ የሰው ልጅ እድገት ደረጃዎች - በሰው ልጅ የሕይወት ዑደት ውስጥ ያሉትን የእድገት ደረጃዎች እና እድገት በተጨማሪም የእያንዳንዱ የእድገት ደረጃ የሚወክለውን የዕድሜ ክልል ያጥኑ።<br>2. ትምህርት 2፡ እርግዝንና እና በግብረ ሥጋ ግንኙነት የሚተላለፉ በሽታዎችን መከላከል - የግብረ ሥጋ ግንኙነት ማድረግ ለምን አይነት አደጋዎች ተጋላጭ እንደሚያደርጉ፣ በተጨማሪም በግብረ ሥጋ ግንኙነት የሚተላለፉ በሽታዎች የሚታዩበት ምልክቶችን ይግለጹ። በግብረ ሥጋ ግንኙነት የሚተላለፉ በሽታዎችን እና እርግዝናን ለመከላከል ከሁሉም የሚበልጠው መንገድ መታቀብ እንደሆነ እና በግብረ ሥጋ ግንኙነት የሚተላለፉ በሽታዎች እንዳይዛመቱ እና እርግዝናን ለመከላከል የተለያዩ የወሊድ መቆጣጠሪያ አማራጮችን መጠቀሚያ መንገዶችን ያስረዱ።<br>3. ትምህርት 3፡ ኤችአይቪን መከላከል እና ህክምናው - ከኤችአይቪ ጋር የሚኖሩ ሰዎች ጤናማ ሆኖ ለመኖር እና የቫይረስ መጠንን ለመቀነስ የሚችሉባቸውን መንገዶች ይገልጹ። በግብረ ሥጋ ግንኙነት የሚተላለፉ በሽታዎችን እና ኤችአይቪን ለመከላከል የባዮሜዲካል አሰራሮች በተጨማሪም የቫይረስ መጠንን መቀነስ ያላቸውን አስፈላጊነትን አንዳንድ ጥቅሞች ይዘርዝሩ። | የትምህርት ደረጃ መስፈርቶች:<br>9.6, 9.9, 9.10, 9.11, 9.12 |
| | <u>ክፍል 2</u>፡ ራስን ማስተዳደር<br><br>በዚህ ክፍል ውስጥ ተማሪዎች ስለ ፆታ እና ስለ ፆታ ማንነት እና ከተፈጥሮዋዊ ፆታ እንዴት እንደሚለዩ ይወያያሉ። እንዲሁም "የፆታ ስክሪፕት" የሚለውን ይገልፃሉ እና ምሳሌዎችን ይመለከታሉ። በመጨረሻም፣ በፆታዊ ዝንባሌ ሶስት ክፍሎች (አቅጣጫ፣ ባህሪ እና ማንነት) እና እርስ በርስ ያላቸውን ልዩነት እና ተዛማጅነት ላይ ያተኩራሉ።<br>1. ትምህርት 1፡ ፆታን መረዳት - ፆታ እና የፆታ ማንነት ምን እንደሆኑ እና ከተፈጥሮዋዊ ፆታ እንዴት እንደሚለያዩ ያብራሩ። የእነዚህን አገላለጾች በርካታ ምሳሌዎችን በማቅረብ "የፆታ ስክሪፕቶችን" ይግለጹ እና ቢያንስ ሦስት የፆታ አገላለጾችን እና እነሱ ሲያድጉ የተቀበሏቸውን መልዕክቶች ይግለጹ።<br>2. ትምህርት 2፡ ፆታዊ ዝንባሌ፣ ባህሪ እና ማንነት - የተለያዩ የፆታ ዝንባሌዎችን ይገምግሙ እና የፆታ ዝንባሌ (አቅጣጫ፣ ባህሪ እና ማንነት) ሦስቱን ክፍሎች እና እንዴት እርስ በርስ የተለዩ እና የተዛመዱ እንደሆኑ ይግለጹ። | የትምህርት ደረጃ መስፈርቶች:<br>9.2, 9.3, 9.4, 9.5. 9.6, 9.7, 9.13 |

| | | |
|---|---|---|
| | ክፍል 3፡ ጓደኝነት<br><br>በዚህ ክፍል፣ ተማሪዎች ጤናማ ያልሆነ ወይም ስሜታዊ ጥቃት የሚፈጽምባቸውን ጓደኝነቶች ባህሪያትን ይተነትናሉ። በየራሳቸው እሴቶች ላይ ተመስርተው የየራሳቸውን የጓደኝነቶች ልኬቶች ምን እንደሚመስሉ ያስተውላሉ። በመጨረሻም ተማሪዎች ፈቃድን የመስጠትን እና ፈቃድ ከመስጠት መታቀብን ማክበርን የማገናዘብ አስፈላጊነት ላይ ያተኩራሉ።<br>1. ትምህርት 1፡ የፍቅር ግንኙነት ጥቃት - ጤናማ ያልሆነ ወይም ስሜታዊ ጥቃት የሚፈጸምበትን ጓደኝነት ባህሪያትን እና ጤናማ ባልሆነ ወይም ስሜታዊ ጥቃት የሚፈጸምበት ጓደኝነት ውስጥ ያለ ሰው ከዚያ ግንኙነት ለመውጣት ምን ማድረግ እንደሚችል ይግለጹ።<br>1. ትምህርት 2፡ ፈቃደኛ መሆን ምን ማለት ነው? - "ፈቃድ"፣ "ግዴታ" እና "አቅም የሌለው" የሚሉትን ቃላት ትርጉሞች ይግለጹ። ፈቃድ በግልጽ የተሰጠበት እና ፈቃድ ያልተሰጠበት ሁኔታዎች መካከል ያለውን ልዩነት ያስረዱ በተጨማሪም ፈቃድን መስጠት እና ግልጽ በሆነ ሁኔታ ማግኘት መከባበር ያለበት ጓደኝነት አካል እንዴት እንደሆነ ያስረዱ። | **የትምህርት ደረጃ መስፈርቶች:** 9.1, 9.6, 9.10, 9.11, 9.12 |
| | **ክፍል 4፡ የግል ደህንነት**<br>በዚህ ክፍል ውስጥ ተማሪዎች ከሕገወጥ የሰዎች ዝውውር ደህንነታቸውን የመጠበቂያ ስልቶችን ይማራሉ። FreeKind Prevention Project ተማሪዎችን ሊያጠቋቸው ካሰቡ ሰዎች እና ሁኔታዎች የራሳቸውን እና የጓደኞቻቸውን ደህንነት ለመጠበቅ እንዲችሉ ለማስታጠቅ የተፈጠረ መሳሪያ ነው።<br><br>1. ትምህርት 1፡ ስለ ሕገወጥ የሰዎች ዝውውር መግቢያ እና አጠቃላይ እይታ - በዚህ ትምህርት ውስጥ ተማሪዎች በጾታዊ ትንኮሳ እና በጾታዊ ጥቃት መካከል ያለውን ልዩነት እና ጥቃትን እንዴት መከላከል እና ሪፖርት ማድረግ እንደሚቻል ያብራራሉ። ስለ ሕገወጥ የሰዎች ዝውውር እና ዛሬ ዓለምን እና ትውልዳቸውን እንዴት እየጎዳ እንደሆነ ይማራሉ። እንዲሁም የሰው ዝውውር እና ብዝበዛ ኃይልን፣ ማጭበርበርን እና ማስገደድን ያካትታሉ።<br>2. ትምህርት 2፡ ለወሲብ ጥቃት ሕገወጥ ዝውውር 101 - ተማሪዎች በአሜሪካ ውስጥ ስለ ሕገወጥ የሰዎች ዝውውር እውነታዎች የተጎጂዎችን፣ የአዘዋዋሪዎችን እና የገዢዎችን መገለጫዎች በመመርመር ይማራሉ።<br>3. ትምህርት 3፡ የሕገወጥ አዘዋዋሪዎች መገለጫ - ተማሪዎች ባህል በአዘዋዋሪዎች ላይ የሚያሳድረውን ተጽዕኖ እና የወሲብ ንግድ ውስጥ ያሉ የወሲብ ንግድ አዘዋዋሪዎች እና አዘዋዋሪዎች መካከል ያለውን ትስስር ይመለከታሉ። ስለ ማለማመድ፣ ስለ ሰብአዊነትን ማቃለል፣ የተለያዩ የዝውውር ሁኔታዎች እና የአሁኑ ባህል የወሲብ ድለላ ባህልን እንዴት እንደሚያራምድ፣ እንደተለመደ እንደሚያደርግ እና እንደሚያሞካሽ ለመማር አራት ክፍሎች ያሉትን አንድ ታሪክ ያጠናሉ።<br>4. ትምህርት 4፡ የብልግና ምስሎች እና ሕገወጥ የሰዎች ዝውውር መካከል ያለው ግንኙነት - ተማሪዎች በብልግና ምስሎች እና በወሲብ ንግድ መካከል ያለውን ግንኙነት ይማራሉ። እንዲሁም በተለያዩ ጥናቶች ላይ የተመሰረተ ስለ ብልግና ምስሎች ሱስ የሚያስይዝ ባህሪ እና በአንጎል፣ በግንኙነቶች እና በማኅበራዊ አመለካከቶች እና ደንቦች ላይ ስለሚያስከትላቸው ተጽእኖዎች ይማራሉ።<br>5. ትምህርት 5፡ የመገናኛ ብዙኃን (ሚዲያ) እና የባህል ተጽዕኖ - ይህ ትምህርት በአሁኑ መገናኛ ብዙኃን፣ በምዕራባውያን ባህል እና በሕገወጥ የሰዎች ዝውውር መካከል ያለውን ግንኙነት ያወያያል።<br>6. ትምህርት 6፡ ተማሪዎች ላይ ያለው ተጽዕኖ እና ተማሪዎችን ማብቃት - ተማሪዎች ስለ ሕገወጥ የሰዎች ዝውውር ያላቸውን እውቀት የሚያሳዩ እና ስለ ጉዳዩ ለሌሎች ግንዛቤ የሚያሳድጉ ፕሮጀክቶችን ይፈጥራሉ። | **የትምህርት ደረጃ መስፈርቶች:** 9.3 |
| | **የFLE መስፈርት ደረጃ በACPS 9ኛ ክፍል የጤና ሥርዓተ ትምህርት ተካቷል 9.8፣ 9.13፣ 9.14**<br>**የFLE መስፈርት ደረጃ በACPS 10ኛ ክፍል የጤና ሥርዓተ ትምህርት ተካቷል 9.2፣ 9.9** | |